# “ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል” (ሆሴዕ 4:6)።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ወቅታዊ ችግር የዳሰሰ ጽሑፍ

በዓለም ላይ ብዙ የእውቀት ዓይነቶች አሉ። ማንም ሰው በደከመበት የሙያ ዘርፍ ባለእውቀት (ኤክስፐርት) የመሆን ዕድል ያለው ሲሆን፣ ከተማረበት ወይም ከሙያው ውጭ ባለው የትምህርት ዘርፍ ደግሞ ጀማሪ ሊሆን ይችላል። ይህን እውነታ ባለመቀበል ከሙያው ውጭ ባለው የእውቀት ዘርፍ ተሰልፎ በድፍረት እንደ ባለሙያ (ኤክስፐርት) መሥራት ቢጀምር ግን የቆመበትን ድርጅት ለክስረት ይዳርጋል፤ የራሱንም ማንነት በሥራው ያጋልጣል። በተመሳሳይ ሁኔታ በመንፈሳዊ እውቀት ያልሰለጠኑ ሰዎችም ያለሙያቸው ሲሰለፉ በቤተ ክርስቲያን ዕድገትና በምዕመናን ሕይወት ላይ ከፍ ያለ በደል ያደርሳሉ፤ ራሳቸውም በሕዝቡ ዘንድ ተመዝነው ይቀላሉ፤ ማንነታቸውን ያጋልጣሉ፤ ከአምላካዊ ፍርድም አያመልጡም።

***መንፈሳዊ እውቀት ምንድር ነው?***

መንፈሳዊ እውቀት የሥነ-መለኮት አስተምሕሮ ሲሆን ይህም ከሞት የታደገንን አምላክ ማንነትና ምንነት ጠንቅቀን የምናውቅበትና የመዳን መንገዶችንም የምንረዳበት የጥበብ ዘርፍ ነው። የዚህ ጥበበ ምንጩ ክርስቶስ ነው። ክብር ይግባውና አምላካችን ክርስቶስ ሰው ሆኖ ለሰው ካደረጋቸው የቸርነት ሥራዎች አንዱ የጨለመውን የሰው ልብ በወንጌል በማብራትና የመዳንን ዕውቀት በመስጠት ሰው ራሱን ከኃጢአትና ከዘለዓለማዊ ፍርድ እንዲታደግ ማገዝ ነው። በክርስቶስ ለሰው ልጅ የተሰጠው ይህ ዓይነቱ መንፈሳዊ ዕውቀት ከሌሎች ጥበባት የተለየ በመሆኑ “የመዳን ዕውቀት” ተብሏል። “የኃጢአታቸው ስርየት የሆነውን የመዳን እውቀት ለሕዝቡ ትሰጣለህ” (ሉቃ 1፡77) ተብሎ ተጽፏልና።

***መንፈሳዊ እውቀት እንዴት ይገኛል?***

የመዳን ጥበበ ወይም መንፈሳዊ እውቀት እንዴት ይገኛል በሚለው ሐሳብ ላይ በኦርቶዶክስና በፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለው ግንዛቤ የተለያየ ነው። የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት በሐዋርያዊ ውርስ (Apostolic Succession) የማያምኑ በመሆናቸው ከአባቶቻችን ተምረን እንወርሰዋለን ብለው ተስፋ የሚያደርጉት እውቀት የለም። ሃይማኖተ አበው በእነርሱ ዘንድ ቦታ የለውም። ስለዚህም የካህናቶችም ሆነ የምዕመናኖቻቸው እውቀት መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ብቻ የተወሰነ ነው። ከኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ጋራ የሚያመሳስላቸው ጥቂት ነገር ቢኖር መንፈስ ቅዱስ ጥበብን ሊገልጽልን ይችላል ብለው ማመናቸው ነው። የፕሮቴስታንት እምነት ከተመሠረተበት ዘመን ጀምሮ መጽሐፍ ቅዱስን በራሳቸው መንገድ በመተርጎም ያለ ማቋረጥ ሲከፋፈሉና በተሳሳተ መንገድ ሲጓዙ የሚኖሩት ከአባቶቻቸው የተረከቡት ወጥነት ያለው የትምህርትና የእምነት መርህ ስለሌላቸው ነው። ጌታ ፈሪሳዊያንን “መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ” (ማቴ 22፥29) በማለት የገሰጻቸው ለዚህ ነበር።

ኦርቶዶክሳዊያን ግን እግዚአብሔር በልዩ ቸርነቱ በተአምራት ሁሉንም የእውቀት ዘርፍ የሚያጎናጽፋቸው ቅዱሳን እንዳሉ ቢያምኑም የአምላካቸውን አፓኘነት ተስፋ በማድረግ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው መማር እንዳለባቸው ይገነዘባሉ። ቅዱሳን ሐዋርያት ዕለት ዕለት በጌታ እግር ስር ቁጭ ብለው ይማሩ እንደነበርና ይልቁንም “ተርጉምልን” (ማቴ 13፡36) እያሉ ይጠይቁት እንደነበር ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል። ለክህነት አገልግሎት ራሳችን ብቁ አድርገን ከመቅረባችን በፊት የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት በመደበኛነት መማር እንዳለብን ከቅዱሳን ታሪክ ብዙ እንማራለን። ታላቁ ሰው ኒቆዲሞስ በልዩ ሙያው የአይሁድ አለቃና የሕግ ምሁር ሆኖ ሳለ ክርስትና ለእርሱ አዲስ በመሆኑ በክርስቶስ እግር ቁጭ ብሎ ይማር እንደነበር ተጽፎ እናነባለን (የሐዋ 3፡1)። ቅዱስ ጳውሎስም በሥርዓት ያስተማረውን ደቀመዝሙሩን ቅዱስ ጢሞቴዎስን ሲመክር “አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር፥ ከማን እንደ ተማርኸው ታውቃለህና” (2 ጢሞ 3፡14) ብሎታል። በተጨማሪም በሐዋርያት ዘመን የነበረው አጵሎስ ለአገልግሎት ከመሠማራቱ በፊት ለእውቀት ያሳየውን ትጋት ሲገልጽ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል “እርሱም በመጻሕፍት እውቀት የበረታ ነበረ። እርሱ የጌታን መንገድ የተማረ ነበረ፥ የዮሐንስንም ጥምቀት ብቻ አውቆ በመንፈስ ሲቃጠል ስለ ኢየሱስ ይናገርና በትክክል ያስተምር ነበር (የሐዋ 18፡25)።

***መንፈሳዊ እውቀት ለማን ይገባል?***

ቅዱስ ጳውሎስ "በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ (ፊልጵ 2:12) ባለው መሠረት እያንዳንዱ ኦርቶዶክሳዊ ራሱን ከኃጢአትና ከዘለዓለማዊ ፍርድ የሚታደግበት እውቀት የሚያስፈልገው ቢሆንም በይበልጥ ግን የክርስቶስን መንጋ ለመምራት ጥሪውን የተቀበሉ ካህናት በቃሉ የበሰሉ እንዲሆኑ ሕግ ቤተ ክርስቲያን ያስጠነቅቃል። በቅዱስ መጽሐፍም እንዲህ ተጽፏል፡ "አንተም እውቀትን ጠልተሃልና እኔ ካህን እንዳትሆነኝ እጠላሃለሁ" (ሆሴዕ 4:6)። "ካህኑ የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነውና ከንፈሮቹ እውቀትን ይጠብቁ ዘንድ ይገባቸዋል፥ ሰዎችም ሕግን ከአፉ ይፈልጉ ዘንድ ይገባቸዋል" (ሚልክ 2፥7)።

***መንፈሳዊ እውቀት የገባው ኦርቶዶክሳዊ ምልክቶች***

- ***መንፈሳዊ እውቀት የገባው አገልጋይ እግዚአብሔርን ይፈራል፤ ሰውንም ያከብራል።*** የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርት አጥብቆ የተማረ ወንጌላዊ ትሁት ነው። በዕድሜ እኩያው የሆነውን ካህን "አንቱ" ብሎ አክብሮ ይጠራል፤ እግዚአብሔርንም ይፈራል። የጥበም መጀመሪያው እግዚአብሔርን መፍራት ነው (ምሳሌ 1:7) ተብሏልና። እንዲህም ባደረገ መጠን ክብሩና ጸጋው ይጨምራል። ነቢዩ እንዳለው "የእውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ያርፍበታል" (ኢሳ 11:2)።
- ***መንፈሳዊ እውቀት የገባው ወንጌላዊ ሰውን አያዋርድም አይሳደብም፤ ተሳስቶም ሲገኝ ቶሎ ብሎ ይቅርታ ይጠይቃል።*** ለምሳሌ ቅዱስ ጳውሎስ ሊቀ ካህናት ሐናንያን "አንተ በኖራ የተለሰነ ግድግዳ" ብሎ ከተሳደበ በኋላ በአጠገቡ የቆሙ ሰዎች ሲጮኹበት "ወንድሞች ሆይ፥ ሊቀ ካህናት መሆኑን ባላውቅ ነው" (የሐዋ 23፡5) በማለት ይቅርታ እንደጠየቀ በሐዋርያት ሥራ ተመዝግቧል።
- ***መንፈሳዊ እውቀት የገባው አገልጋይ ለክርስቶስ መንጋ ይራራል፤*** እንደ ሙሴ "አሁን ይህን ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው፤ ያለዚያ ግን ከጻፍኸው መጽሐፍህ እባክህ ደምስሰኝ አለ" እያለ ለሕዝቡ ይጸልያል። የክርስቶስ እንደራሴ ነውና "የጠፋውንም ይፈልጋል፣ የባዘነውን ይመልሳል፤ የተሰበረውንም በንስሐ ይጠግናል፣ የደከመውንም ያጸናል (ሕዝ 34፡16) እንጅ አያሳድድም፤ አያወግዝም።

***በፕሮቴስታንት መንፈስ የተቃኘ የክህነት አገልግሎት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እያስከተለ ያለው አዳጋ፤***

በውሸት እውቀትና በገንዘብ ዓለም እየናጠች ያለቻው የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን አረማውያንን ከማጥቃት ይልቅ ኦርቶዶክሳዊያንን ማጥመድ ልማዷ ስለሆነ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥቃት ከመቶ ዓመታት በላይ እንደ ጅብ ዳር ዳሩን እየዞረች መንጋውን ስታስደነበር የቆየች ቢሆንም የጥረቷን ውጤት ማየት የጀመረችው አሁን ነው። ይኸውም የፕሮቴስታንት መርህ የሆነው በመደበኛ ትምህርት ሳይሆን በማንበብ ላይ የተመሠረተ የውሸት እውቀትና የገንዘብ ፍቅር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመስፋፋቱ ነው። ቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎታቸው በእውነተኛ እውቀትና በመንፈሳዊ ጥበብ ላይ ሳይሆን በስሜትና በገንዘብ ፍቅር ላይ የተመሠረተ ወንጌላውያንን አፍርታለች። በመሆኑም፤

1) ***በአግልጋዮች መካከል መወነጃጀልና መጠፋፋት ተጀምሯል፤***

   ቤተ ክርስቲያኒቱ በውሸት እውቀት ለተካኑና በገንዘብ ለበለጸጉ መንፈሳዊ መሰል ነጣላ ለባሾች እጅ ሰጥታለች። በዚህም ምክንያት ልጆቿን አስተምራና መክራ የመመለስ አቅም አንሷት ከአንዱ እጅ ዱላ ተቀብላ ሌላውን እየደበደበች ማባረር ጀምራለች። ለታላቁ ክብር ያበቃቻቸው ሊቃነ ጳጳሳት የባዘነውን መመለስ አቅም አንሷቸዋል፤ መንጋውን መምራት ተስኗቸዋል። ይህ ትልቅ ውድቀት ነው። እነዚህ ነጠላ ለባሾች ራሳቸው የኦርቶዶክስን አስተምሕሮ እያዛቡ ሌላውን ተሐድሶ እያሉ የሚያባርሩት ምክንያት የገንዘብ ምንጫቸው እንዳይደርቅባቸውና ተቀናቃኝ እንዳይኖራቸው ስለፈለጉ ብቻ ነው።

2) ***የቤተ ክርስቲያኒቱን ወጥነት ያለው ኦርቶዶክሳዊ አስተምሕሮ ማስጠበቅ ከማይቻልበት ደረጃ እየተደረሰ ነው።***

   በመደበኛው የሥነ-መለኮት ትምህርት ቤት ሳይማሩ ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው "በውሸት እውቀት" (1 ጢሞ 6፡20) ራሳቸውን ከሊቃውንት ጎራ ያሰለፉ ወንጌላውያን አገልግሎታቸው በእውቀትና በመንፈሳዊ ጥበብ ላይ ሳይሆን በስሜት ላይ የተመሠረተ ነው። በዚህም ምክንያት እውነተኛውን ኦርቶዶክሳዊ አስተምሕሮ ለመቀበል

ሕሊናቸው ግትር ወይም ዳተኛ ከመሆኑም በላይ ትምህርታችሁ የተሳሳተ ነው ሲባሉ በድፍረት አባቶች ሊቃነ ጳጳሳትን መሳደብና ማዋረድ ይጀምራሉ። ቀርበው መከራከርም አይፈልጉም። ማንነታቸው ይገለጻልና። የቤተ ክርስቲያንን እውነተኛ አስተምሕሮ ተከትለው ሳይሆን ስሜታቸው በመራቸው ይጓዛሉ። ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለ "ወንድሞች ሆይ፥ የልቤ በጎ ፈቃድና ስለ እስራኤል ወደ እግዚአብሔር ልመናዬ እንዲድኑ ነው። በእውቀት አይቅኑ እንጂ ለእግዚአብሔር እንዲቀኑ እመሰክርላቸዋለሁና። የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ የራሳቸውንም ጽድቅ ሊያቆሙ ሲፈልጉ፥ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም" (ሮሜ 10፡3)።

ጥርት ያለውን የኦርቶዶክስ ትምህርት በመማርና በማስተማር ፋንታ አንዱ ሳይዝላቸው ሲቀር ሌላውን እያመጡ ስለ ማተብና ነጠላ አለባበስ፣ ስለ ወር አበባ፣ ስለ አሳማ ሥጋ እንዲሁም ስለ ኦርጋን እየሰበኩና የባልቴት ተረት እያወሩ 25 ዓመት አለፋቸው። ይህም መጨረሻ በቅርቡ እንደታየው በቤተ ክርስቲያንን የዶግማ ትምህርት ላይ ወሳኝ ጥያቄ ሲነሳ ቤተ ክርስቲያንን መወከል የማይችሉ ውስን እውቀት ያላቸው ለገንዝብ የሚተጉ ቱጃሮች መሆናቸውን በግልጽ አሳይቷል። እነርሱ የሚጓዙበት መንገድ በውሸት እውቀትና በገንዝብ ፍቅር ላይ የተመሠረተ <u>የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ለኦርቶዶክስ የዘረጋችው የጥፋት ወጥመድ</u> ሆኖ ሳለ አበው ሊቃነ ጳጳሳትን የሚሳደቡት፣ አባቶች እርስ በራሳቸው እንዲለያዩና እንዲወጋገዙ የሚያደርጉት ከዚህም አልፎ የቤተ ክርስቲያን ልጆችን "ተሐድሷዊ ፕሮቴስታንት" እያሉ የሚያሳድዱት ማንነታቸው እንዳይገለጥና የገንዘብ ምንጫቸው እንዳይደርቅ የግል ተከታዮቻቸውን ለማብዛት ነው። ከየትኛውም የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቤት እንዳልተማሩ እየታወቀ ይህን ሁሉ በድፍረት የሚያደርጉት ሕዝቡ የማያነብ ያልተማረና የነገሩትን ሁሉ የሚቀበል የዋሕ ነው ብለው ስለሚገምቱ ነው።

ኦርቶዶክሳዊያንን የሚቃወም ሰባኪ የኦርቶዶክስን ካባ ያጠለቀ ፕሮቴስታንት ነው እንጅ በምንም መልኩ ኦርቶክሳዊ ሊሆን አይችልም። አንድ ኦርቶክሳዊ አገልጋይ በመድረክ ላይ ስድብን አያስተናግድም፤ ሰዎች ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በውግዘት ሲለዩ ይጸልያል እንጅ ጮቤ አይረግጥም። እውነተኛ የክርስቶስ እንደራሴ መንጋው ሲሸሽ የቤተ ክርስቲያን ግቢ ሲራቆት ማየት አይፈልግም። ስለ አንዲት ነፍስ መለየት ያዝናል ያለቅሳል እንጅ የቤተ ክርስቲያን ልጆችን ለማሳደድ ዱላ አያቀብልም። ስለዚህ ሰውን እያወገዘና ስድብን እየዘራ በመድረክ ላይ በፕሮቴስታንት መንፈስ የሚጮኽ እንዲህ ዓይነቱ ሰባኪ ለገንዘብና ለግል ዝና የቆመ የውሸት ሰባኪ ነው። ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንን አይወክልም።

ውድ ኦርቶዶክሳዊያን!! ኦርቶዶክሳዊት እምነታችሁን አጥብቃችሁ ያዙ እንጅ በማንም ተረት ተረት አትታለሉ። እውነትን ለማወቅ ተማሩ፣ ጠይቁ፣ ተከራከሩ እንጅ አባቶቻችሁን አትሳደቡ፤ መርገምን ትሸምታላችሁ። ውሸተኞች ውሸታቸው እስከሚገለጥ ድረስ ቢዝነሳቸውን ያጧጡፋሉ፤ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንን ግን ያዳክማሉ። ስለዚህ እናንተ እውነትን አውቃችሁ ለእውነት ትቆሙ ዘንድ ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለ፣ "በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ። ለእርሱ አሁንም እስከ ዘላለምም ቀን ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን" (2 ጴጥ 3፡18)።

የቅዱሳን አምላክ እግዚአብሔር ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንን ይጠብቅ፤ አሜን።